# አላምጠው የማይውጡትን አይጎሰጉሱም

የሃገራችን ችግር ሁሉም እየተነሳ አዋቂም እኔ ነኝ፤ ሃገርም ከእኔ በቀር ሲል አንተ ድግሞ ምን ትባላልህ አንልም። ሁሉም ተጠሪ፤ ሁሉም ሹም፤ ሁሉም ፖሎቲከኛ፤ ሁሉም ዲሞክራሲና ሁሉም ሁሉንም ነኝ ሲል ሌሎቻችንስ አይባልም። መሳቂያ ሆነው መሳቂያ ማድረጋቸውንም አላወቅን። ስልጣን ካልያዙ ትምህረት፤ ዕድገት፤ ሥራ አጥነት፤ ድህነትና የሃገር ሰላም አይቸግራቸውም። ሕዝብን ሳያውቁና ሳያውቃቸው ለሃገር ቆመናል ይላሉ። አቅማቸውን አጎልብተው የደጋፊ አቅም ሳያጎለብቱን በውጭ ፍርፋሪ እየተንከላወሱ ስለሃገር ኢኮኖሚም ያወራሉ። የአካባቢያቸውን እንኳን ሰው ሳያውቁ ዘጠና ሚሊዮን ህዝብ እንወክላለን ሲሉም አያፍሩም። ነገረ ስራቸው ሁሉ የዕውር የድንብር መሆኑንም አላወቁኢተ። ሌሎቻችንም ለምን አንልም። ግን እስከ መቼ?

ከእነዚህም የተከበሩ የአቶ ግርማ ሰይፉ መጣጥፍና የፓርቲዎች ነን ባዩች ከማንም በላይ መሆን "አላምጠው የማይውጡትን" አባባል አሰታወሰኝ። ሁሉም ነቅቶ ይሄማ እንዴት ይሆናል እንዲል። በተጨባጭ ለማየትም በቅድሚያ የተከበሩ አቶ ግርማን መጣጥፍ ቃኝተን ወደ ፓርቲነን ባዮች እንመለሳላን። የተከበሩ የፓርላማ አባል በአዲስ አበባ የአንድ አካባቢ ተመራጭ መሆናቸውን ዘንግተው በሃገር አቀፍ ጉዳይ ስለ ቤቶች፤ ሽብርተኝነት፤ ሃይማኖት፤ ስራ አጥነት፤ ስደተኝነት ፓርላማ ውሎ፤ ወዘተ ይጣጥፋሉ። ከማንምና ከምንም በላይ ከሆኑ አይቅር እንዲህ ነው። ምክንያቱም አንድም ሰውዬው ሁሉንም ያውቃሉ አለያም ጥናት ያደረጉ አማካሪዎች አሏቸውና በሚቀጥለው መጣጥፍ ችሎታቸውንና የአማካሪዎቻቸውን ብዛትና ተግባር ቢነገሩን? ካልሆነ የመረጣቸውን ሕብረተሰብ ችግር አወያይቶና ተወያይቶ እንደመፍታት የሀገሪቱን ተግብር ሁሉ አውቃለሁ ባይ መሆን ሁሉንም ሳያላምጡ መጎስጎስ መሆኑን ያሳውቋል።

በመሠረቱ ሃገራዊ ጎዳይ በሚመለከተው የፓርላማ ንዑስ ኮሚቴ ስለሚታይ ይሳተፏል እንጅ በማያውቁት የሽብርተኛ ሕግ ላይ ጊዜን ማባከን የሌላንም ጊዜ ማጥፋት እንደሆነም ያስተምሯል። ምክንያቱም በቅድሚያ አቶ ግርማ ሠይፉ የሕግ ባለሙያ ባለመሆናቸው ስለ ሽብርተኛ ሕጉ መናገር አይችሉም። እውነተኛ ፖለቲከኛ ከሆኑ በፓርላማ ንዑስ ኮሚቴ በኩል ይጨርሷል። ችግር ካለ መረጃውን ይዞ በመሞገት ተቋሙን ማስተካከልም እኮ የሃገርን ድርሻ መወጣት ነው። በሁለተኛ ደረጃ ስለሃገራችን ድህንነት መረጃ ስለሌላቸው መጣጥፋቸው የተለቀመ ወሬ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ሕጉ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ ዓለም አቀፍ ይዘቱን ጠብቆ በፓርላማ የተወሰን በመሆኑ አቶ ግርማ ሠይፉም ሆኑ አሮጌዎቹ ፖለቲከኞች (ሽማግሌ የተጣላ የሚያስታርቅ፡ የተለያዬ የሚያቀራርብና ዳኝነት የሚሰጥ ነውና ለፖለቲከኞቻችን አይመጥንም) እና መሰሎቻቸው አይቀልዱበትም። የሽብርተኛ ሕጉ ከድህነት አሮንቃ ለመውጣት ጥረት የምታደርግ ሃገራችን የውጭ ባለሃበቶችና ሃገር ጎብኝዎች መዋዕለ ነዋያቸውን ሃገር ውስጥ ለማስገባት እንዲችሉ ሰላምና ድህንነታቸው ከሚረጋገጥባቸው መሣሪያዎች አንዱ ነውና። ሰላምና ደህንነት ደግሞ የሕዝብና የመንግስት ችግር እንጅ የሃገርን በድህነትና ትርምስ መሟቅቀ ለሚናፍቁ የወሬ አርበኞች እንዳልሆነ ለፓርላማ አባል ነኝ ባዩና መሰሎቻቸው ማስተማር ግድ ይላል። አራተኛ በዓለማችን አክራሪዎች ጥፋት ከሚያደርሱበት ድርጊት አንዱ ሽበር መሆኑን አቶ ግርማ ዘንግተውት ሳይሆን የውጮቹ የአማርኛው ሬዲዎና ፓልቶክ አስተናጋጆችን ለማስደሰታና ድጋግመው መቅረብ እንዲችሉ ነው። "ብቸኛው" መባሏን ይወዷታል።

ለመሆኑ እጃቸው ከጥፋት የጠራ ከሆነና እንደ እነ ግንቦት 7 ላሉ ባሉበት የሚረግጡ አሸባሪዎችና መሰሎቻቸው ድጋፍ ለመስጠት ካልሆነ በስተቀር የሽብርተኞች ሕጉ ምን ያስፈራል? በሀገር ላይ ጦር የመዘዘን መደገፍ እኮ በየትኛውም ዓለም በሃገር ክህደት በሞት ያስቀጣል።

ሌላው አቶ ግርማ ሠይፉ ደሴ ከተማ ላይ በጠሩት ስብሰባ ሰልፈኛው የሸህ ኑሩን ሞት የተፈበረከ እያለ ሲጮህ እኔና ፓረቲዬን አይማለከትም ከማለት ይልቅ "የእኛ ማርቲን ሉተር ኪንግ ከየት ይሆን? ግርማ ሠይፉ ማሩ" በሚል ርዕስ *"... ስለዚህ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ... በተለይ ሌሎች ክርስቲያኖችን በማጥፋት እናድርገው እያሉ ከሆን መረጃ ይሰጡንና አብረን እንታገላቸው። ይህ ነገር ካለ በእውነት አክራሪነት አለ ብለን ልንስማማ እንችላለን መፍትሄም በጋራ ማፈላለግ አለብን ብዬ አምናለሁ።..."* በማለት ለማላገጥ የሞከሩት። በቅድሚያ ህዝብ ይተላለቅና ከዚያ አብረን እንታገላለን መሆኑ የሆን? ወይንስ የሰላም አስተማሪውን ሸህ ኑሩን የእኔን ትምህረት ተቀብልህ ሌሎችን ካላስተማርክ ብሎ መግደል ጥፋት አይደለም እዬተባለ? ታዲያ እየተስተዋለና በልክ ይሁን አይባልም ትላላችሁ?

አቶ ግርማ ሠይፉ በዚሁ መጣጥፋቸው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሆን ተቃውሞ የለኝም ብለዋል። ሰውዬው ድብቅ አጀንዳ ካልያዙ በስተቀር ስልጣንና ሃይማኖት በህብረ ብሄሯ ኢትዮጵያ አወያይቶ አያውቅም፤ አሁንም አያወያይም፤ ወደፊትም አያወያይ። በዘጠና ሚሊዎን ሕዝብ መሃል ሰውዬው እራሳቸውን እንዴት አዩት ይሆን? እንደ እውነቱ ከሆነ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ችግሩ ሃይማኖት ሳይሆን የነበረን ባህል፤ ወግና እምነት ለማጣፋት መሞከር። በአፍጋኒስታንና ማሊ እንደ ደረሰው ጥፋት ለብዙ መቶ ዓመታት ተጠበቀው የቆዩ ቅርሶችን ማፍረስ፡ ሰረቀ ብሎ እጅ መቁረጥ፤ ሴትና ወንድ ግንኙነት ቢያደርጉ በድንጋይ ድብድቦ መግደል የመሳሰሉ ጭካኔና አክራሪነትን ነው። እውን አቶ ግርማ ይህንን አያውቁም ወይንስ ይህች "ብቸኛው የፓርላማ ሰው" የምትለዋ ታፔላ አዘናጋቻቸው?

ስለዚህ አቶ ግርማና መሰሎቻቸው እንደመጣላቸው ቢናገሩ አላምጠው የማይውጡትን ጎስጉሰው የሚጨናነቁት እነሱ ራሳችው እንጅ እኛን አይመለከተንም አንበል። ቀደም ባሉት ፖለቲከኞች እንደታዬው እራሳችን ላይ እናውጣችሁ ይሏቸው የነበሩ አሽቃበጮች አውርደው እንደከሰከሷቸው የአቶ ግርማም ጉዞ ወደዚያው ነው መባልም የለበትም። ምክንያቱም የአቶ ግርማ ሠይፉ አባባል ወኔውን

አጥተው እንጅ የ”ድምጣችን ይሰማዎቹን” እንጉርጉሮ ከአሜሪካኖቹ መሰሎቻቸው ኮፒ ለማድረግ ነው። አሁን አሁን እንደ ፋሽን በተያዘው አረብ ሲጮህ አብሮ መጮህ፡ ፈረንጅ የተናገረውን እንደ ቅዱስ ቃል ማነብነብና የሌላውን ኮፒ ማድረግ አባዜ ከተጠናዎታቸው ወገኖቻችን አንዱ አቶ ግርማና መሰሎቻቸው “ሰላማዊ” የሚል ታፔላ የተለጠፈባትን የጥቂት አክራሪዎች ሰልፍ የመኮረጅ ዳር ዳር ነው። ግን ሰላማዊ ሰልፉን እኮ መንግሥት ይፈቅዳል። የሚፍቅደውም የኢሕአዴግን በሕዝብና በፖለቲካው መጎልበት በመተማመንን እንጅ የተበታተኑ ፖለቲከኛ ነን ባዮች ስንዝርም እንደማይራመዱ ቀድሞም ያውቀዋል። ስለዚህ ለአቶ ግርማ ወደዱም ጠሉ እየጎለበተ በመጣው የሃገራችን ፓርላማ ጉያ ተሸጉጠው አሉባልታ ሲነዙ ትዕግስቱ ለመረጣቸው ሕዝብ ይቆማሉ በሚል እንጅ ማረሙ እንዳልተዘነጋ ያሳውቋል።

ከሁሉም በላይ ሽብርተኝነት ድምበር የለሽ አጥፊ አካል በመሆኑና ሃገራት መረጃ ስለሚለዋወጡ  አሜሪካና ኢትዮጵያም ይተባበራሉ። ይህም ለኢትዮጵያ ሰላምና ደህንነት በማሰብ ሳይሆን የአሜሪካንን ፓስፖርት የያዘ ሁሉ (ለሃገር ቆሜአለሁ እያለ በየመንደሩ የሚፎክረውን ዲያስፖራ ጨምሮ) የሽብርተኞች ኢላማ በመሆኑ የዜጋዋን ደህንነት ለማረጋገጥ ነው። ለምሳሌ ቀደም ሲል እ.ኤ.አ፣ በ1998 በታንዛኒያና ኬንያ የደረሰው የሽብር ጥቃት ለሁለቱ ሃገሮች ያለመ ሳይሆን አሜሪካንን ለማጣቃት ነበር። በመሆኑም ጥፋቱ በሃገራችን እንደማይደርስ ለማሳየት የሽብርተኞች ሕጉ ከዓለም አቅፍ ሕግጋት ጋር ታናቧል። ስለዚህ ሃገራችን ወዳጅን ለማረጋጋትና ድህነትን በሰላሟ ማረጋገጫ መሣሪያነት ለመዋጋት ደፈ ቀና በምትልበት ወቅት የአቶ ግርማና ቃል አቀባይ የሆኑላቸው አካላት በሽብርተኛ ሕጉ አይቀልዱበትም። እቅጩንም ይነግሯል።

ሌላው የአቶ ግርማ ጥረት የእወቁኝ አባዜ ለመሆኑ “የቃሊቲ እንግልት” የሚለውን የቅርብ መጣጥፋቸውን ይቃኟል። እንግልት ሲሉ ግን ለሕዝብ አይደለም። *“…ሲጠቃቀሱ የነበሩት ዘቦችን ጠጋብዬ በቀልድ ዓይነት ልክናችሁ በቴሌቪዥን የምታዩኝ ግርማ ነኝ ብዬ ተቅላቀልኳቸው። መዋሸት ጀመሩ እኛ ስለአንተ አልተነጋገርንም ብለው በአንድ ዋሹ…”* ይላል መጣጥፋቸው። ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነና ውሸት ከነበረ የዋሹት አቶ ግርማ ናቸው። ምክንያቱም ሰውዬው የቴሌቪዥን ይሁኑ የራዲዎ ወይንም ፓልቶክ ችግሩ የራሳቸው እንጅ የሌላ አይደለም። አይሆንምም። እርስ በርሳችሁ ስለ እኔ ተነጋገራችሁ ስል አዎ አላላችሁምና ውሸታሞች ናችሁ ማለትስ ምን ይባላል? ሐቁ ግን አቶ ግርማ ተራ በመያዝ ክብራቸው የተነካ መስሏቸው ስለተቁነጠነጡና የማረሚያ ቤት ጥበቃዎቹም የተለዩ እንክብካቤ አድርጉ የሚል መመሪያ ስለሌለቸው ምን እናድርግ በሚል ተወያዩ እንጅ ስለ አቶ ግርማ ማንነት አልገደቿቸውም። ነገሩ ኢህአዴግ ነው ያሉትን ሁሉ መስደብ ሙያዬ ብሎ የያዘውን ዲያስፖራ ለማስደሰት ይመስላል። ለመሆኑ በቴሌቪዥን/ፓልቶክ መቅረብ በሕዝብ መታውቅ ነው ያለው ማን እንደሆነ አቶ ግርማ ሠይፉ ይጣጥፉ ይሆን?

ተሳሳቱ እንጅ አቶ ግርማ አንድም ከፓርላማው ለሚመለረከተው ሁሉ የሚል ድብዳቤ ቢያዙ ኖሮ ቀይ ምንጣፍ ተዘርጎቶ በጠበቃቸው። ያለበለዚያ የፓርላማ አባልነት የሚያሳይ አንገት ላይ የሚንጠለጠል መታወቂያ ቢያደርጉ ኖሮ እሳቸውም አይነገላቱ ሠራተኞቹም ዋሹ አይባሉ። የሚያሰጋው ግን ነገ አቶ ግርማ የግል ቡና ቤት ገብተው እኔ በቴሌቪዥንና ፓልቶክ የምታውቁኝ የፓርላማ አባል በመሆኔ የሚስማማኝ ይሄኛው ጠረንጼዛ ነውን ይለቀቅልኝ እንዳይሉ። ለነገሩማ ለፓርላማ አባልነት ለመረጠው ህብረተሰብ የሚበጅ ልማትና አስተዳደር ተግባራዊ በማድረግ አኩሪ ፖለቲከኛ ከመሆን ይልቅ በእንቶ ፈንቶ መጣጥፍ ጊዜውን ከሚያባክን ምን ይጠበቃል?

በመሆኑም የሚመለከተው ፓርላማ ንዑስ ኮሚቴ ግለሰቡን አቅርቦ የሃይማኖት መጠፋፋት ካለ ይነገረንና እኛም እንተባበር የሚለው ማላገጫ የፓርላማ አባል ቋንቋ አይደለምና ሃሳባቸውን ያብራሩ። በሁለተኛ ደረጃ በማረሚያ ቤት በትግባር ላይ በነበሩ የታራሚ ጥበቃ ሰራተኞች የተሠራው ድራማ የማን አለብኝ የሥልጣን ብልግና (“ኮራብሽን (corruption)”) ነውና መልስ ይስጡ። በሶስተኛ ድረጃ የደሴ ሰልፍ ተሳታፊዎች የሸህ ኑሮ ሁሴን ሞት ተፈበረከ ካሉና አቶ ግርማም የለሁበትም ካላሉ የሚያውቁት ሌላ አካል አለ ማለት ነውና ቢያሳውቁ? ምክንያቱም በደህንነት ምርመራ ሽብርተኞቹ በቁጥጥር ስር ውለዋል። የአቶ ግርማ ሰይፉ መጣጥፍ ግን የተያዙት ሽብርተኞች አይደሉም ዓይነት ስለሆነ እሳቸው የሚያውቁት ነገር አለ ነውና ለፍትሕ አሰራሩ ቢተባበሩ? የሃገር ደህንነት የሚቀለድበት ሳይሆን ከፍተኛ ሃላፊነት በመሆኑና አቶ ግርማ ድግሞ የሃላፊነት ሰው ባለመሆናቸው። አላምጠው የማይውጡትን አይጎሰጉሱ አይደል? እግረ መንገዱን ፓርላማው መቀለጃ እንዳልሆነ ግንዛቤ ያገኙበታል። ለሌሎች አጉራ ዘለሎችም ጥሩ ትምህርት ይሰጣል። ቀሪውም እየተነሳ እንደመጣለት የወሬ ጥሩንባ አይነፋም።

መልዕክቴም አላምጠው የማይውጡትን መጎስጎስ መጨረሻው ራስን በራስ ማፈን ነውና የባሰ እንዳይመጣ ሁሉም በልክ ይሁን ማለትን እንልመድ ለማለት ስለሆነ የኢህአዴግ ደጋፊ መጣጥፍ ምንትሴ የሚለው ብልጣብልጥነት አይሰራም። መሞከሩም ድፍረት ነው። አባባሉም እኮ የመንደር ታጋዩ ዲያስፖራ መጨፈሪያ መዝሙርም ነውና መሻማትስ አይሆንም ብላችሁ? ቢሆንስ አንገት በሚያስደፋው ርሃብ ላይ የዘመተ መንግሥት ያልተደገፍስ ማን ሊደገፍ ኖሯል? ህዝብን አስተባብሮ የሃገራችን ማፈሪያ የነበረውን ርሃብ የሚፋለም መንግሥት ቀርቶ ለአንዲት ሃገር ከሰላሳ በላይ ፓረቲ ነን ባዮች እርስ በርሳቸሁ በጋራም ይሁን በቡድን እየተፋተጋችሁ ደጋፊ አለን ትሉ የለ? ምክንያቱም ሰላሳ ፓርት ማለት በምርጫ ውቅት ደጋፊውን ለሰላሳ

መከፈልና አንድ ተመራጭ ባቀረበ ፓርቲ መሸነፍ ነው። ሰላሳ ፓረቲ ማለት አምባገነንነት፤ ያለመተማመን፤ ያለመደማመጥ፤ መናናቅ፤ ለራስ ብቻ መቆም፤ አቅጣጫ አልባነት፤ እንደው በጥቅሉ ሌላ ሳይሆን አቅጫ የጠፋበት መንገደኛ ነው። እናስወግድ የሚትሉትን ኢሕአዴግ ለመታገል ያልተባበራችሁ መቼና እንዴትስ ልትተባበሩ? ብዛታቸሁም በየትም ዓለም የሌለና መንግሥት ብትሆኑ ባለሙያ፤ ባለስልጣን፤ ተጠሪ፤ ሚኒስቴር፤ አስተዳዳሪ፤ መምሪያ ሃላፊ፤ ወዘት ከየት ይመጣልስ አይባልም? ምክንያቱም ለሰላሳ ፓርቲ የሚሆን ባለሙያና ምሁር አይኖርም ቢኖርም የሃገር ተግባርና ጎዳይ ሰው አላባ የሆናል። ሰላሳ ቦታ ተፈረካክሶ ስለአንድነት ሲሰበክም አይታፈርም። መተግበር ቀርቶ ሊታሰብም እንደማይችል ያልተገነዘባችሁ እናንተና አቀንቃኞቻቸሁ ብቻ እንጅ ወደድንም ጠላንም በሌላው ዓለም መሳቂያና መሳለቂ ነን። ለዚህም መንግስት ራሱ ሃላፊነት አለበት። ምክንያቱም መመዝገቢያ መስፈርቱን ለምሳሌ የአባላት ብዛት፤ የገቢ መጠንና ምንጭ፤ የሚሸፍኑትን አካባቢ ወዘተ በአገባቡ ባለማስቀመጡ ፓርቱዎች እየተፈረካከሱ ሌላ ፓርቲ ሰለሚመሰርቱ (ሰማያዊ ፓርቲ ይጠቀሳል) ነገ ሃገሩ ሁሉ ባለፓርቲ እንዳይሆን ያሰጋልና።

ፖለቲከኞቻችን አሁንም ስላለፈው ምርጫም እስኪሰለችን ደጋግማችሁ በምታነሱት ዘጠና ዘጠኝ በመቶ ያሸነፈ መንግሥት ለሚለው መዝሙራችሁ ከኢሕአዴግ ጋር ስትወዳደሩ አንድ ለሰላሳ ሰለነበር ያኔ ቀርቶ ለሚሊዮን ዓመትም አንደማታሸንፉ ትምህርት ውሰዱ። ይህም የእናንተና የእነወሬ ስነቁ ዲያስፖራ ፖለቲከኞች ደካማነትና ድንቁርና እንጅ የሌሎቻችን እንዳልሆነ አቶ ግርማና ፓርቲዎች ንን ባዮች ተገንዝበው አላምጠው የማይውጡትን አፍ ውስጥ መጎስጎስ አደጋና እራስን በራስ ማፈን መሆኑን ቢገነዘቡ?

ለእነሱም የአቅም ማወቅ ለእኛም እረ አይሆንም ድፍረት ይልመድብን!!!

ዓለም ገ/እግዚአብሄር